የምፅዓቱ መጽሐፍ ቅዱስ HOLY BIBLE የምሥራች

| ቅጽ 84 ቁጥር 2(980) |

“እኔ መንገድና እውነት ነኝ” (ዮሐንስ ወንጌል 14÷6)

ክርስቶስ በእኔ ይኖራል (በአንድሪው ሞሬ)

ክርስቶስ እግዚአብሔር እንደሚወደው እንድንኖር እንዴት ይረዳናል? ብዙውን ጊዜ ክርስቶስን ከእራሳችን በመለየት እንደሚረዳን እናስባለን። ነገር ግን እራሱ ክርስቶስ እንዳስተማረን እኛ እና ክርስቶስ የአንድ ዛፍ ግንድ እና ቅርንጫፎች ያህል የተያያዝን አንድ ነን። *“እኔ የወይን ግንድ ነኝ። እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ” (ዮሐንስ 15÷5)*። የወይን ግንድ እና ቅርንጫፎቹ ካላቸው ቅርበት የበለጠ ምን ቅርበት ሊኖር ይችላል? በዚህ በተመሳሳይ መልኩ የእኛ እና የክርስቶስ ቃልና ሕይወት የተያያዘ ሊሆን ይገባዋል። *“ለዘለዓለም በሚኖረው ክርስቶስ አዳኝነት ልንኖር እራሱ በሰማይ እንዳለ ዛሬውም ከእኛ ጋር እንደተሰፋ ቃሉ እንደሚኖር ልናምን ይገባናል” (ማቴዎስ 28÷20)*።

ኢየሱስ ክርስቶስ በቃሉ እና በመንፈሱ ሁሌም ወደ እኛ እንደሚመጣ እንመን። ክርስቶስ አምላክም ሰውም አማላጅም ተማላጅም መሆኑን ቅዱስ ቃል እንደሚያረጋግጠው በሁሉም ሥፍራ በሁሉም ጊዜ እንደሚኖር አምነን በእምነት እንመላለስ።

ነፍሳችን በክርስቶስ ስትሞላ ምንም እንኳን በሥጋ ብንኖርም እኛ ያለን ሕይወት ሰማያዊ እና የክርስቶስ ሕይወት ነው፤ ቅዱስ ቃሉ እንደሚለው በክርስቶስ ያመንን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር የተሰቀልን የሞትን የተነሳን እና ዘለዓለም የምንኖር ነን። *“ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ እኔም አሁን ሀያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል። አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝ እና ስለእኔ እራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው” (ገላትያ 2÷20)*።

እሰይ አሁን ኑ ወደመንፈስ ወደቃሉ በክርስቶስ ኑሩ!

እኛ በእምነት ያለን ሁሉ በእራሳችን የእራሳችንን ኑሮ አንኖርም። የምንኖረው የምናደርገው በጎ ነገር ሁሉ በእኛ በሚኖረው በክርስቶስ የሚከናወን ነው። *“እኔ ከእራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም” (ዮሐንስ 5÷30)*

ከመጀመሪያው ጀምሮ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ዘንድ የነበረ እራሱ እግዚአብሔር አምላክ የሆነ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ የተፀነሰ የተወለደው እና አድጎ ያስተማረው ያገለገለው የተሰቀለው የሞተው እና ከሙታን በድል የተነሳው እና ወደሰማይ ያረገው ለዘለዓለም በእግዚአብሔር ቀኝ የሚኖረው እና በክብር የሚመለሰው የእኔ ሕይወት እምነት መሠረት ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሁልጊዜ የአባቱን ፈቃድ የተከተለው እና የፈጸመው ለእኛ እርሱን እንደአባት ምሳሌአችን ሆኖልን እንድንመስለው እና ያዘዘንን እንድንፈጽም ነው። (ዮሐንስ 3÷35፣ 5÷26)

እግዚአብሔር የሰጠንን ሕይወት የሚያሥፈጽመን እራሱ እግዚአብሔር በአንድያ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። የእምነት ሥራ ቃልኪዳን ነው። (ዮሐንስ 3÷16)

እኛ ወደእግዚአብሔር የምንቀርበው በአንዳች መልካም ሥራችን ሳይሆን እራሱ እግዚአብሔር

ባዘጋጀልን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ባገኘነው እምነት እና ፀጋ ብቻ ነው። (ኤፌሶን 2፥8፣ ዮሐንስ 3፥16)

ጌታ ከእናቱ ለቅድስት ማርያም እንደተናገረው ለእኛም ትልቅ ምሳሌ የሆነው የእግዚአብሔር መሆናችን እና ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ቤት መኖራችን ይሆናል (ሉቃስ 2፥49)። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊፈጽም ወደዚህ ምድር መምጣቱን እንደተናገረ እኛ፣ በዚህ ምድር የምንኖረው እና የምንሠራው ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ነው (ዮሐንስ 6፥38) የእግዚአብሔር ፈቃድም ሰውን ማዳን ነው (ሉቃስ 3፥6)

የክርስቶስ ትንሳኤ የእኛም ትንሳኤ ነው

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስደንቅ መለኮታዊ ሥራው ከተፀነሰ ጀምሮ ታላላቅ ተዐምራቶችን ሠርቶ በሮማውያን መዳፍ ሥር ወድቆ ተገርፎ ለስቅላት በቅቷል።

ይህንን ያደረገው ለአህዛብ ገዢዎች እና ዛሬም ለማያምኑ ሽንፈት ቢመስልም ለእኛ በወንጌሉ ለምናምን ትልቅ ድል እና ሞትን ለዘለዓለም ማሸነፊያ እምነት ነው (1ኛ ቆሮንቶስ 1፥18-21)።

ስለዚህ በዘመናት ሁሉ ክርስቲያን አማኞችም ሆነ የብሉይ የእግዚአብሔር ሰዎች ተስፋቸውን የሚያድስ ትንሳኤን አግኝተዋል። እኛም በኢየሱስ ክርስቶስ ባለን እምነት ምንም በሥጋ ተስፋችን ቢጠፋም በእምነታችን በጌታ ሁልጊዜም ትንሳኤ ይኖረናል።

በአንዳች ተስፋ መቁረጥ ምድር ብትናወጥ ዓለም ብትተረማመስ ቅድስና ቢጠፋ ያመኑት ሳይቀር ቢክዱ ቢኮበልሉ እኛ ግን ከማይጠፋው ዘር ዳግም የተወለድን መቼም ተስፋ ትንሳኤ አናጣም። ጌታ ይክበር! (2ኛ ቆሮንቶስ 4፥8)

የኢየሱስ ክርስቶስ ልዩ ብቃት እና ዘለዓለማዊ ታላቅነት (በዮናታን ኤድዋርድ)

“ማንም የተጠማ ቢኖር ወደእኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፉ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል” *(ዮሐንስ 7፥37)*

ዓለማዊ ሰዎች የሚያደርጓቸው ምድራዊ ጠፊ ነገሮች ደስታ እንደሚሰጡ ያምናሉ። ሆኖም ግን በእነዚህ ምድራዊ ነገሮች ተሟልቶላቸው ዘወትር ደስታ እያጡ አንዳንዶችም የከፋውን እራስን የማጥፋት ጉዳት ይፈጽማሉ።

እኛ ግን በዚህም ምድር ሆነ በሚመጣው ልዩ ብቃት እና ታላቅነት ያለውን የክርስቶስ ዘለዓለማዊነትና እጅግ ልዩ ታላቅ ብቃት እንመሰክራለን እንከተላለን። የእግዚአብሔርን ፀጋ እና ምህረትም እንተገብራለን።

የክርስቶስ ብቃት የሥጋ ፍላጎት ብቻ ግብ ያደረገ ሳይሆን ሥጋን፣ ነፍስን እና አእምሮን ያካተተ ጊዜአዊ ሳይሆን ዘለዓለማዊ እርካታን የሚያቀዳጅ ልዩ ችሎታ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በዓለማችን ካሉ መጽሐፍት ሁሉ የተለየ በየዕለቱ ሲነበብ አዳዲስ ትምህርቶች መገለጦች ምሪቶች የሚሰጠው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት ዘለዓለማዊ ኃያል የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ነው (ዮሐንስ 6፥50፣ ጢሞትዎስ 3፥16)

የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሰው የማይሰጠው እናት እንኳን ለወለደችው ልጅ ከምትሰጠው ፍቅር በላይ የዘለቀ ልዩ ፍቅር ነው። እናት ምንም ብታፈቅር ሰው ስለሆነች ትረሳለች ትደክማለች ትሞታለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን መቼም የማይደክም የማያርፍ የማይረሳ

የማይተኛ የማያንቀላፋ አባት እናት ወንድም እኅት ንጉሥ መሪ ሆኖ ከአማኝ ልጆቹ ጋር ለዘለዓለም የሚኖር ነው (መዝሙረ ዳዊት 94፥1፣ 121፥4፣ ኢሳይያስ 49፥15፣ ዕብራውያን 13፥5)።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእራሱን ሕይወት ሳይሳሳ ለሚወዳቸው አማኝ ልጆቹ የሰጠ ማንም የሃይማኖት መሥራች ያልፈጸመውን ያከናወነ ጌታ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ያለምንም የዘር የጾታ የፖለቲካ የሕይወት መስተጋብር ልዩነት ሳያደርግ የሚያፈቅር የሚቀበልና የሚያድን ነው። (ቆላስያስ 3፡11)

ይህንን ልዩ የፍቅር ጌታ ከማወቅ ከመከተል ከማመንና ለሌሎችም ይህንን ከመመስከር የሚበልጥ ምን ደስታ ይኖራል? ምንም። እንግያውስ እንነሳና እንመስክረው!

እነሆ ሰውየው !

የእሾክ አክሊል በራሱ ላይ በማድረግ ብዙ ከገረፉትና ደሙ ከአካሉ በሚንጠባጠብበት ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሮማ ወታደሮች ወደገዢው ጲሊጦስ ባቀረቡት ወቅት ጲሊጦስ *"እነሆ ሰውየው"* የሚለው ቃል ያ ሰውም አምላክ የሆነውን ጌታችንን በሚገባ የሚገልጽ ቃል ነው።

በዚያ ዘመን በነበረው ልማድ እንዲህ የሚገለጽ ሰው ከሰዎች የተለየ ሰውን ለማስተዋወቅ የሚጠቀሙበት ቃል ሲሆን መጥምቁ ዮሐንስ ታላቁ ነብይ እንዲህ ጌታችንን ገልጾት ነበር። *"እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያሰወግድ የእግዚአብሔር በግ" (ዮሐንስ 1፡29)*

ዛሬም ሆነ ባለፉት የቤተክርስቲያን ታሪክና ዘመናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነሆ ብለው ያስተዋወቁ የመሰከሩለት የተሰውለት እጅግ ሚልዮኖች ሲኖሩ ዛሬም በምድራችን ይገኛሉ። ትልቁ ቁምነገር በእርሱ መንፈስ እነሆ ጌታችን እነሆ አዳኛችን እነሆ ተስፋችን ብሎ በእውነት በመንፈስ ከመመስከርና ከመኖሩ ላይ ነው።

እስኪ የኢየሱስ ክርስቶስን ትህትና ገርነት ፍቅርነት ምህረት ሰላማዊነት ሁሉን ተቀባይነት እንደገና እያሰላሰልን ይህን በጎ ባህርያት እንዲያፈስልን እንማጸነው።

የሚገርፉትን የሚወጉትን የሰቀሉትን ይቅርታ የሚያደርግ በዚህች ምድር ላይ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስተቀር ፈጽሞ አልታየም።

ይሰቀል ይሰቀል ብለው ለዘበቱበት ከሳሾቹ አይሁድና ጭፍሮቻቸው ሳይቀር ምህረቱን የገለጸ ጌታ በዚህ ዘመን በቂም በጥላቻ የእርሱን ስም በያዙ ሳይቀር የተሞሉትን ቢያይ ምን ይለን ይሆን? እነሆ በደጅ ቆሜአለሁ ያለን ጌታ ልባችንን በቃሉ በመንፈሱ እየቀሰቀሰና እንከፍትለት ከክፉ መንገዳችን ተመልሰን የሰላም አለቃ የፍቅር ጌታ የምህረት ጌታ የሆነውን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልባችን ወደ ቤተሰባችን ወደ ከተማችን ወደሀገራችን እናስገባው። (ዮሐንስ ራእይ 3፥20)

ጌታዬ ለእኔ አንበሳና በግ ነው (በዮሐንስ ሚለር)

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው" (መዝሙር 23፥1)

እረኝነት በቅዱሳት መጻሕፍት የፍቅርና የእንክብካቤ አገልግሎት መጠሪያ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን መልካም

የብሉይ ኪዳን ልምድ በእራሱ አንደበት "መልካም እረኛ እኔ ነኝ" በማለት ለተከታዮቹ አስተምሮናል። (ዮሐንስ 10÷11)

በምሥራቁ የዓለም ክፍል የበግ እረኛ ከበጎቹ ጋር የተቆራኘና አብሮ የሚኖር ነው። (ይህንን በትውልድ ሀገራችን በኢትዮጵያ በደብረ ብርሃንና አካባቢው ተርጓሚው አይቻለሁ።)

በጎቹ ለአደጋ እንዳይጋለጡ እረኛው እጅግ የሚጠነቀቅ ሲሆን ማንኛውም የበጎቹን ጥቃትና አደጋ እረኛው በንቃት ይከታተላል። እረኛው በጎቹን ያውቃል እነርሱም ድምጹን እየሰሙ ይከተሉታል። ይህም የእረኛችን ጌታን ድምጽ እያወቅን እየሰማን በእርሱ ሀሳብ ለምንጓዝ ግልጽ ሲሆን ድምጹን ሳንሰማ የተጎዳንበት ሌሎችም በክፉ አውሬ የተበሉትን እናውቃለን።

በጎቹን ከእጇ ማንም አይነጥቃቸውም ብሎ ጌታ የገባልንን የተስፋ ቃል በማመን በእርሱ እቅፍ ለዘለዓለም እንድንኖር ልንተጋ ሌሎቹን ልናስተምር ይገባል። (ዮሐንስ 10÷28)

እንደዚሁም ሁሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ለአማኝ ልጆቹ አንበሳ፣ ታዳጊ፣ ንጉሥ መከታ ነው። (ራእይ 5÷5)

የይሁዳ አንበሳ የሚል ስም የተሰጠው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕብራውያን ይሁዳ ክብር ምስጋና የሚገባው ማለት ሲሆን ወደፊት በክብር የሚመጣው ጌታን በዮሐንስ ራእይ በይሁዳ አንበሳ ገልጾታል።

ጌታችን እንደ በግ የዋህ ሆኖ የተገለጸበት እኛም በየዋህነት እርሱን ጌታችንን ሰምተን እንድንከተል ሲሆን እንደአንበሳ የተገለጸው ደግሞ ዳግም ሲመጣ ሊዋረድ፣ ሊሰቀል፣ ሊገረፍ ሳይሆን በድል፣ ሠይጣንን ለመጨረሻ ጊዜ ሊቀጣ እኛንም በዘለዓለም ቤቱ ሊሰበስበን በክብር እንድንቀበለው የሚያተጋን ቃል ነው። ማራናታ ጌታችን ሆይ ቶሎ ና! (ራእይ 22፡ 29)

የክርስቶስ የደሙ ኃይል እና ድል

"በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን ነውርና እድፍ እንደሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ" (1 ጴጥሮስ 1÷18)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰልን ከፍተኛውን መስዋእትነት የሚሳይ ነው። የመቤዠት ትልቁ ምልክት ደም የሚፈስበት መሆኑን የብሉይ ሥርዓት በተደጋጋሚ የተገለጸው በመቃኑ ላይ የበጉ ደም እየተረጨ እስራኤላውያን ከሞት መልአክ ያመለጡበትን የሚያሳስብ ሲሆን ጌታም ደሙን ያፈሰሰው በዚያ የፋሲካ የብሉይ መታሰቢያ ቀን ምሽቶች ነበር። (ዘጸአት 12፣ ዮሐንስ 6÷53፣ 19÷31)

በደሙ ውስጥ ሕይወት አለ የሚለው የብሉይ ኪዳን ቃል እንዲፈጸም የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተስፋ ቃል ሆኖ ኃይልና ድልን ላመኑት ሁሉ ይሰጣል። (ዘሌዋውያን 4÷3፣ 17÷11፣ 1ኛ ዮሐንስ 1÷7)

የበጉ የክርስቶስ ደም ልክ አፉን ሳይከፍት ክፉ ሳይወጣው የተሰዋልን ጌታችንን ትህትና የጌታን ፈቃድ የአባቱን ፈቃድ ልክ እንደ ይስሀቅ ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኖ የተሰዋበት ለእኛ ለአማኝ ክርስቲያኖች የበጉ ደም ትልቁ ኃይላችን ድላችን ነው። (ዕብራውያን 9÷22፣ ራእይ 12÷11)

የበጉ ደምና ኃይል በእምነት ለሚገኙ ሁሉ የሚሰጥ እንጂ በዘር ከብሉይ የደሙ ቃልኪዳን ጋር ለተያያዙ ዕብራውያን የተሰጠው በአዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ ከነገድ ከዘር ከወገን ለተጠሩት ሁሉ የሚከናወን ሆኖ በደሙ ከነጹት በመጨረሻው ከሁሉም ዘርና ወገን

በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይሰበሰባሉ። (ራእይ 7፡9)

በኢየሱስ ክርስቶስ በበጉ የደም ሥርዓት ነጻ የምንወጣው አማኞች በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን አሸናፊ መስለው ገናና መስለው በምድራችን ላይ ከሚፈራረቁ መንግሥታት ኃያላን በላይ ለመሆናችን ቅዱስ ቃሉ ያረጋግጥልናል። *"በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። ሞት ቢሆን ሕይወትም ቢሆን መላእክትም ቢሆኑ ግዛትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቻለሁ።"* *(ሮሜ 8፡37-39)* አሜን ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው (በኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ)

"እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል። በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል። ነፍሴን መለሳት ስለስሙም በጽድቅ መንገድ መራኝ። በሞት ጥላ መካከል እንኳን ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም፤ በትርህና ምርኩዝህ እነርሱ ያጸናኑኛል። በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ። በጠላቶቼ ፊት ለፊት ራሴን በዘይት ቀባህ ጽዋዬም የተረፈ ነው። ቸርነትህና ምህረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተለኛል፤ በእግዚአብሔርም ቤት ለዘለዓለም እኖራለሁ።" (መዝሙረ ዳዊት 23፡1)

እግዚአብሔር እረኛዬ ነው ብል በመንፈስ ቅዱስ እየተመራ ይህንን እጅግ የተወደደ የሚያጽናና መልእክት ያቀረበው ንጉሥ ዳዊት እረኝነትን በሕይወቱ ያለፈበት ልምዱን ከማንም በላይ የሚያውቅ ነው። እረኝነት ለሚመሩት መንጋ ሕዝብ ትልቅ ፍቅር ርህራሄ ደግነት የሚታይበት ለመሆኑም እራሱ የእምነታችን ጀማሪና ፈጻሚ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን መልካም እረኛ እኔ ነኝ ብሎ የገለጸበት ቅዱስ ቃል ዋና ዋቢያችን ነው። *"መልካም እረኛ እኔ ነኝ"* (ዮሐንስ ወንጌል 10፡11)

እረኝነት በቤተሰብ በመንደር በከተማ በሀገር በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከሰት አመራር ሲሆን ጌታችን እንዳስተማረው የእርሱን ፈለግ የሚከተሉ መልካም እረኞች ያሉትን ያህል ክፉ እረኞች ለመንጋው ለሕዝቡ ግድ የማይላቸው ሕዝቡንም ራሳቸውንም ለጥፋት የሚዳርጉ በዘመናት ሁለ ታይተዋል፤ ዛሬም ይታያሉ። የክፉ እረኞች ልዩ መለያ ለሚመሩት ፍቅር የጎደላቸው ክፋት መከራ በመጣ ጊዜ ሕዝባቸውን የማይጠብቁ ራስ ወዳዶች መሆናቸው ነው። (ዮሐንስ ወንጌል 10፡11)

የእግዚአብሔር ሕዝብ መልካም እረኛ ወይም ንጉሥ እራሱ እግዚአብሔር ሲሆን የእግዚአብሔር ሕዝብ ምሳሌ የተደረገው የአይሁድ/ እስራኤል ማህበረሰብ የእግዚአብሔርን መሪነት ችላ በማለት በአህዛብ ልማድ ንጉሥ ፈልጎ እንደተፈቀደለት ነገር ግን የከፋ መከራ እንደገጠመው ቅዱስ ቃሉ ይመሰክራል። (1ኛ ሳሙኤል 8)

ዛሬም እግዚአብሔር አልተለወጠም በኢትዮጵያም ሆነ በአሜሪካና በመላው ዓለም የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ንጉሥ እራሱ እግዚአብሔር ነውና በምንም በማንም ሳንስት የእግዚአብሔር መሪነትን በሕይወታችን በሀገራችን በቤተክርስቲያናችን እንለማመድ እናክብር።

የክርስቶስን ፍቅር ማወቅ (በአርተር ፒንክ)

“ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶናን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ” (ኤፌሶን 3፡19)

የክርስቲያን እጅግ ተፈላጊ መሠረታዊ ጉዳይ ሕይወቱ በክርስቶስ ፍቅር መሞላቱና መያዙ ነው። ይህ የክርስቲያን ፍቅር ብቃቱም እግዚአብሔር አብ ከልጁ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ባለው ፍቅር ተምሳሌት እኛንም እንደሚያፈቅረን የገለጸበት ሕያው ቅዱስ ቃሉ ነው። (ዮሐንስ 15÷9) *“አብ እንደወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ”*

ይህንን ልዩ መውደድ ፍቅር እኛ የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር በስተቀር ከየትም አናገኘውም።

የእግዚአብሔር ፍቅር ወረት የማያውቅ ሁኔታዎች የማይለውጡት ዘለዓለማዊ ልዩ ድንቅ ፍቅር ነው።

እግዚአብሔር በዚህ ፍቅር እኛ አማኞችን ለማፍቀሩ ቅዱስ ቃሉ የገለጸው የአማኞች ጎብረት የሆነችው ቤተክርስቲያን ባፈቀረበት ፍቅሩ ውስጥ እኛ ክርስቲያኖች የተጠቃለልን መሆኑ ነው። (ዘጸአት 19÷5፣ ኤፌሶን 5÷27)

ለቤተክርስቲያን ለእኛ ለአማኞች በክርስቶስ በኢየሱስ የተገለጠው ፍቅር ልዩ ሰማያዊ ፍቅር ነው። ይህ ፍቅር ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲጠራ ለአማኞች የተሰጠ ስጦታ ነው።

የእግዚአብሔርን ፍቅር ለማወቅ እና ለመቅመስ በእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ መሞላት መነካት መለወጥ ይሻል። ስለፍቅር ብዙ ግጥሞች እና ዜማዎች ማቀናበር ቢቻልም እውነተኛውን የእግዚአብሔር ፍቅር የሚፈጥርና በሰዎች ላይ የሚያሰፍን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሆነ ማመን ብቻ የሚገኝ ነው። (ዮሐንስ 3÷16)

የእግዚአብሔር ፍቅር አስተማሪና ሠጭ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያንን ፍቅር ለመግለጽ በዚህ ምድር ሳለ በሕይወቱ በባርያነት አገልግሎቱ እና በመጨረሻም በዘመኑ የነበረውን አስከፊ የመስቀል ቅጣት በመቀበል ለእኛ አስተላልፎልናል፣ *“ነፍሱን ስለወዳጆቹ ከመሰጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም”* (ዮሐንስ 15÷13) (ፊሊጲሲዮስ 2÷7)

ይህ የክርስቶስ ፍቅር ሰዎች በስሙ ፍቅራቸውን በእውነት የሚገልጹበት እንጂ በስሙ የሚያታልሉበት የሚሸጡበት ማስመሰያ አይደለም።

ክርስቶስ የእርሱ የሆነውን እውነተኛ ፍቅር በሕይወታችን በማህበራችን በሀገራችን እና በዓለማችን እንዲያፈስልን በብርቱ ጸሎት እንማጸነው።

መስቀሉ መሠረታዊ ጉዳይ ነው (በኤቶዘር)

የክርስቶስ መስቀል በክርስትና ሕይወት ትልቁ መሠረታዊ ለውጥ አምጪ ጉዳይ ነው። የጥንቱ የሮማውያን መስቀል ዜጎቻቸው ያልሆኑት ለጥፋታቸው የሚቀጡበት የሚሰቀሉበት ሲሆን የማ.ሰቀለው ሰው በመስቀል ተሰቅሎ ከቆየ በኋላ ሲገደል ጌታ ግን የተገረፈው የተሰካበት እሾክ ደሙን ካፈሰሰ በኋላ በፈቃዱ ነፍሱን በመስቀል ላይ መስጠቱ የተለየ ያደርገዋል። ይህ በሮማውያን የመስቀል ቅጣት ታሪክ የመጀመሪያው ሆኗል።

ጌታችን በመስቀል መቀጣቱ ወንጀለኛ ሮማዊ ያልሆነ የሚቀጣበት በመሆኑ አይሁድ የመስቀልን ቅጣትና ምልክት ዛሬም ድረስ ይፀየፉታል፣ ያርቁታል (ተርጓሚው የታዘባቸው የመስቀልን ምልክት በሚላክላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዳይገኝ የሚከለክለው የአይሁድ መንግስት በእስራኤልና የሙስሊሞቹ መንግስታት ስለሆኑና መስቀል የሌለበትን አዲስ ኪዳን ለመላክ ተገደናል። ሌላው የሞርሞን ሃይማኖት እንዲሁ የመስቀል ምልክት መዋረድ በመሆኑ እንደማይቀበሉ መሪያቸው ነግሮኛል።)

የክርስቶስ መስቀል ለእኛ ለአማኝ ክርስቲያኖች ከጌጥ ምልክትነት በላይ የተከፈለንን ክቡር የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ስቃይና መከራ እያስታወስን እርሱን በማመን በመከተል የሚደርስብንን የዚህ ዓለም መከራና ስቃይ ያስታውሰናል። (ማቴዎስ 10÷38፣ ሮሜ 3÷25፣ ሉቃስ 9÷23፣ ገላትያ 2÷20)

ለመስቀሉ ክርስቲያኖች ሁለት ነገር ይጠበቅባቸዋል። ቃሉን በመታዘዝ የዘለዓለም ሕይወትን መጠበቅ፣ እስከ ሞት መከራን መቀበል ወይንም የመስቀልን መከራ በመፍራት ጌታን መካድና ለዘለዓለም ማፈር ናቸው። (ማቴዎስ 10÷33፣ ያዕቆብ 1÷12፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4÷8)

በዘመናችን የሚታየው ከመስቀሉ ቃል የሚጋጭ የፍቅረ ነዋይ የምኞት ስብከትና ልምምድ ከመስቀሉ ቃል የሚጣረስ ክፉ ልምምድ ስለሆነ ልንርቀው ልንጸየፈው ይገባናል።

በመስቀሉ ቃል ጸንተን በእምነታችን ዘወትር በመታደስ ይህችን ጠፊ ዓለም ሳንመስል ሥጋችንን ገዝተን ከሠይጣን ወጥመድ ተጠብቀን በጌታ እንድንኖር ዘወትር እራሳችንን እንፈትሽ እንታደስ። (ሮሜ 12÷3)

እውነተኛው የወይን ግንድና የመስቀሉ ቃል
(በሮይና ሪቪል ሄሰንና በአል ዊቲንግል)

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ ብቻውን የሰው ዘርን ከጥፋት ለማዳን መፈጸም ቢኖርበትም ሰዎችን ተባባሪ ሠራተኛ ያደረገው ባለው ልዩ ፍቅር ነው።

በዚህ ልዩ የእግዚአብሔር ፍቅር ጌታ ሰዎችን አጋር ያደረገበትን እራሱን ግንድ እኛ አማኞችን ቅርንጫፎች ያደረገበት ትምህርቱና አሠራሩ ነው። *“እኔ የወይን ግንድ ነኝ፣ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።” (ዮሐንስ 15÷5)*

የቤተክርስቲያን አገልግሎትም ሆነ የብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት በሕብረት በመስማማት በመንፈስ ቅዱስ አንድነት የሚከናወን እንጂ ያንድ ሰው አምባገነንነት የሌለበት መሆኑን ይህ የጌታ ቃል ያስተምረናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ ይህንን ይደግፋሉ። ግለሰቦች በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ መቆየት እየተሳናቸው ለብዙ መከፋፈልና ልዩነቶች የጌታ ቤት መዳረጉን ከጥንተ ቤተክርስቲያን ታሪክ ጀምሮ እንረዳለን። ስለዚህ እኛ አማኞች እርስ በርሳችን የአንዱ ግንድ የክርስቶስ ቅርንጫፎች መሆናችንን ተቀብለን ያንዱ መጎዳት የሌላው መሆኑን በመረዳት በእርስበርስ ፍቅር መደጋገፍ የጌታን ቤትና መንጋውን እንጠብቅ። (ኢሳይያስ 5÷21፣ 1 ቆሮንቶስ 1÷10፣ ኤፌሶን 4÷3)

የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚያስተምረው ጌታችን እርሱ ቃል የሆነው መሠረታዊ የእምነታችን ማእከል ሲሆን ያንንም በመስቀሉ ላይ ፈጽሞታል። የመስቀሉ ቃልንም ሐዋርያው አብራርቶልናል። (1ኛ ቆሮንቶስ 1÷18)

ይህ የመስቀሉ ቃል በየዘመናቱ ከመስቀሉ የጌታ መልእክት ውጭ በተጻራሪነት ሲሰበክ ኖሯል። ዛሬም የመስቀሉ ጠላቶች ቃሉ

በሚላቸው የክርስቶስ ቃል ለጥፋት ለጭቆና ለባርነት ለብዝበዛ ይውላል።

እኛ ይህን ከቅዱስ ቃሉና ከቅዱስ መንፈሱ የተረዳን የመስቀሉን ቃል በተገቢው መንገድ ማስቀመጥ የቤተክርስቲያን ተሃድሶ መሪ ማርቲን ሉተር እንዳለው ወደ መጽሐፍ ቅዱስ እንመለስ ብለን በድፍረት ልንነሳ ልንተጋ ይገባናል።

ዓለም አቀፍ የጸሎት ርዕሶችና ምስክርነቶች ማሳሰቢያዎች

ከማሌዢያ

ጋዜጣችሁ የነፍሴን እርካታ አስገኝቶልኛል። ያለማቋረጥ ትልኩልኝ ዘንድ አጠይቃለሁ።

ከጃማይካ

በየጊዜው በምትልኩልኝ የምጽዓቱ የምስራች እባረካለሁ። በተለይ በሐምሌና ነሐሴ 2017 እትም እጅግ ተጽናንቻለሁ፤ ተባረኩ።

ከቦንጋ/ኢትዮጵያ

የምጽአቱ የምሥራች ከወጣትነት ጊዜ ጀምሮ ዛሬም በአገልግሎት ብዙ የጠቀመኝ መንፈሳዊ ምግብ ነው። በዚህ ላሉት ማካፈል እንድችል ተጨማሪ ኮፒዎች ላኩልኝ።

ከአሪገን - አሜሪካ

የምጽዓቱ የምሥራች የእምነት ጽናት ይሠጠኛል። ለአገልግሎቱ የአቅሜን በሚቀጥለው ወር እልክላችኋለሁ። ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ።

የደህንነት ምክሮች

1. ኃጢያተኛ ስለመሆናችሁ ለእግዚአብሔር ተናዘዙ። (ሮሜ 3፥23፣ 6፥23)
2. የእግዚአብሔርን ይቅርታ ተቀብላችሁ ፊታችሁን ወደጌታ መልሱ (ኢሳይያስ 55፥7)
3. በክርስቶስ ጌታና አዳኝነት በማመን ሕይወታችሁን በሙላት አስረክቡት በቅርብ ወዳለ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ወደ ሚያጠምቁ ተቀላቀሉ (ሐዋርያት ሥራ 2፥38፣ ማቴዎስ 28፥19)

ለአማርኛው አንባቢዎች

ይህንን መንፈሳዊ ጋዜጣ የምትከታተሉ ሁሉ ለምትልኩልን የጸሎት ድጋፍና ምስጋና እናመሰግናለን። በግል ለእያንዳንዳችሁ መላክ ስለማንችል በዚሁ የጌታ ሰላም ይድረስላችሁ። የአገልግሎቱ ብቸኛ ገቢ የአንባብያን ስጦታ በመሆኑ የምትችሉትን በፖስታ ቤት በኩል ለተጠሪ ብርሃኑ ጥርሰማ በመላክ ተባበሩን።

ጌታ አምላክ ሀገራችን ኢትዮጵያን እንደተስፋ ቃሉ (መዝሙረ ዳዊት 67፥31) እንዲጎበኛት ጸሎታችሁ በብርቱ ይቀጥል።

ተርጓሚና አስተባባሪ

ቄስ ቻፕሊያን ኤዲ/አደፍርስ ሀብቴ መካሻ/

የምጽአቱ የምሥራች የወንጌል መነቃቃት አገልግሎት

ዋና አሳታሚ ሪች ካርማይክል

Publisher: Rich Carmichael

የአማርኛው አስተባባሪና ተርጓሚ ኤዲ/አደፍርስ/ ሀብቴ መካሻ

Coordinator:- Eddie Habte Mekasha

ሥርጭትና ክትትል ብርሃኑ ጥርሰማ

ጽሕፈት ሥራ አቤኔዘር ጽሕፈት ሥራ

አርትአት BK Designs

የፖ.ሣ.ቁ/ P.O.Box 8986

ስልክ ቁጥር 0993154034

በሶላር ማተሚያ ቤት ታተመ

Printed by Solar Printing Press

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

በነጻ የሚታደል!